ይድረስ ለአባ ቀውስጦስ
<u>ባሉበት፣</u>

ባሉበት ያልንበት ምክንያት ኢትዮጵያ ነው ያሉት ሲባል አሜሪካ፣ አሜሪካ ነው ያሉት ሲባል ደግሞ ኢትዮጵያ ስለሚሆኑ እንዲሁም በጤና ነዎት ስንል "በሽተኛ ነኝ" ስለሚሉ ነው። በእርቅ ለትውልድ የሚበጀውን የፍቅርና የአንድነትን የቤተክርስቲያን ተግባር በኢትዮጵያ ሲኖዶስ ጉባዔ ተገኝተው ከመሟገት ይልቅ ከዚህ ቀደም በሲኖዶሱ ጉባዔ በግምባር ቀደምትነት እጅዎን በማውጣት እንደ ቅዱስ መንፈስ ትዕዛዝ ሳይሆን እንደ ስጋዊ ሰው ያበላሹትን ተጸጽተው ለማስተካከል ከእውነተኛ አባቶችና ከወንድሞች ጋር በሕብረት ከመቀመጥ ይልቅ "ከዚህ ቀደም ቀጠሮ ይዣለሁ" በሚል ሰበብ አስቀድሞ በተቀነባበረ በበሽታ ሰበብ በአንድ ሬስቶራንት ባለንብረት ቤት መገኘትዎትን ተመለከትን።

ታመሙ ብለን ስናዝን በሲኖዶስ ጉባዔ ተገኝተው ሰላምን ለመከታተልና ለመወያየት የካዳው መንፈስዎና ጉልበትዎ እዚህ አማሪካ መጥተው "አባ ጳውሎስ እርቁን አይፈልጉም" ማለትዎን ስንሰማና በቨርጅኒያ ኪዳነ ምሕረት ቤተ ክርስቲያን ዲያቆን  ሰርግ ላይ ከአጋፋሪዎችዎ ጋር ሲንጎማለሉ አይተን አይ ሀገሬ ኢትዮጵያ ሰው አይውጣብሽ ተብለሽ ተረገምሽን? ለትውልድ እንቅፋት የሚሆን ሰው ላታጭ? አልና ለቃሉ ሰግደን ልዑል እግዚያብሔር ፍርድህ አሳየን ብለን ተማጸንን።

እንደተለመደው የማስመሰያ እንባዎትን ከማማጥዎ በፊት ይብላኝልዎት ብለን እርስዎ የሚገኙበት ቤት የቁሳር ለቅሶ ቤት መስሎ ስለታየን፣ ዐይን ለዐይን እያዩን ጥለንዎት ሄደናል። ምክንያቱም እርስዎ ባሉበት ከዚህ ቀደም እኛም እያየን በምንወዳትና ለብዙ ምዕመናን መጠጊያና አለኝታ በነበረች በዲሲ ቅድስት ድንግል ማርያም ቤተክርስቲያን የተናገሩት ከባለቤቶቹ ፖለቲካኞች የበለጠ ፖለቲካኛ ስሜትና ሃሳቦች እስከዛሬ ድረስ ቤተክርስቲያኒቷን ከማትወጣው ችግር ላይ ጥለዋታል። አሁንም እርስዎ ባሉበት ሀፍረትና ችግር አይቀሬ ነውና አሁንስ ተነቃቃን! በዚህ አጋጣሚ ቤተክርስቲያናትም እርቅን፣ ሰላምንና ይቅርታን የጠሉትን፣ የገፉትንና የረገጡትን ማናቸውም በአባት ስም ባያስተናገዱ ችግሩን ከውዲሁ ለመከላከል ይበጃል እንላለን።

ከላይ የተመለከተውን ካስገነዘብን በኋላ አሁን አባ ቀውስጦስን ልንጠይቅዎት የምንፈልገው "በውኑ ይህ ቤት ፈርሶ ሳለ እናንተ እራሳችሁ በተሸለሙ ቤቶቻችሁ ለመኖር ጊዜው ነውን" ሀጌ ም. 1 ቁ. 4 እንዲሁም "እግዚያብሔር በደስታ የሚሰጠውን ይወዳልና እያንዳንዱ በልቡ እንዳሰበ ይስጥ" 2ኛ ቆሮ. ም. 9 ቁ. 7 በሚለው የአምላካችን ቃል መሪነት በእምነታችን እንዳናፍር ለበጎ  ሥራ ሁሉ በደሥታ ስለእምነታችን ነገር በእየሩሳሌም የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን ገዳማት እድሳትና ለቦታዎች ማስፋፊያ ከዚህ ቀደም በእርስዎ በአባ ቀውስጦስ አማካይነት በርካታ ገንዘብ በተለያዩ ጊዜያቶች በውጭ አገር ከሚገኙት ምዕመናን ቅዱስ ሲኖዶስ ጭምር ገንዘብ መለመንዎትና መሰብሰብዎት ይታወሳል።

ይሁን እንጂ ገዳማትን በግምባር ተገኝተን እንዳየናቸው ያኔ እንደነበሩ ከዓመታት በኋላ አሁንም ሁኔታው እጅግ አሳዛኝና ችግሩ የከፋ ሆኖ ተመልክተን አዝነናል። እንደተዋህዶ ልጅነታችንም ጉዳዩ ያገባናል፣ ይመለከተናልም። ስለሆነም የተዋጣው ገንዘብ ለተጠየቀበት ዓላም ባለመዋሉ ወይንስ ሌላ? ገንዘቡ የት ደረሰ? በምን ሁኔታ ላይስ ይገኛል? ለምንስ እስከ አሁን ለታቀደለት ተግባር አልዋለም? በገዳማቱ ያሉት የመጸዳጃ ቤቶች ሽታ እንኳ የማያስጠጋ ሆኖ ለመነኮሳቱ የጤና ጠንቅ፣ በዚህ በሰለጠነ ዓለም ለጎብኚዎች አሳፋሪ ከመሆኑም በላይ ኢትዮጵያን ለምታህል ታላቅ አገር መዘበቻና መሳለቂያ ለምዕመናኑናም ለመላው የአገሪቱ ዜጋ አንገት መድፊያ ሆኗል። አይ አለመታደላችን! በሰንቱ ነገር እንፈር?

አባ ቆውስጦስ ሰሞኑን እንደገና ካረፉበት መጥተንም ካየንዎት ከአስራ አምስት ቀናት በፊት እዚህ አሜሪካ መጥተው ልደታ ቤተክርስቲያን ለተሰበሰበው ምዕመናን "እዚህም እዛም ነኝ" ብለው ተናግረው ወደ ግሪክ ጌጥ ለመግዛት ካቀኑት ከአባ ገብርኤል የመኝታ ክፍል ሆነው ባሉበት መልስ እንዲሰጡበት በትህትና እንጠይቃለን። ከዚህ በኋላ ማየት ማመን ነውና ምዕመናኑ በቦታው ያየነውንና የሰማነውን ማስረጃ በማስደገፍ እናቀርባለን። ምናልባት ለገዳማት የሆነ ግዥ ተፈጽሟል እንዳይባል ከገዳሙ ከራሱ ወጭ ሆኖ እንደተሸፈነ የሚጠቁሙ ማስረጃዎች ስላሉ የተጣራና የሚጨበጥ መልስ እንዲሰጡን በትህትና እንጠይቅዎታለን።

ክብርና ምሥጋና ለልዑል እግዚያብሔር ይሁን!

ግንቦት 27 ቀን 2000 ዓ.ም.

ተቆርቋሪ ምዕመናን
ከሰሜን አሜሪካ